# ምስጋና - ለቅንጅት አለም አቀፍ አመራር አባላት

ለክቡር ዶ/ር ሞገስ ገብረማርያም

ለክቡር አቶ ብርሃነ መዋ

ለክቡር አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ

ለክቡር ዶ/ር ገብርዬ ወልደሩፋኤል

ለክቡር አቶ ዳንኤል አሰፋ

ለክቡር አቶ ዳዊት ከበደ

ቅንጅት አለም አቀፍ አመራር ከተመሰረተበት፤ ወርሃ ግንቦት 2006 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጁላይ 27 2007 ዓ.ም ድረስ የፈጸመው ታላቅ ተግባር በታሪካችን በክብር የሚዘከር ነው። በተለይም የቅንጅት መሪዎች በእስር ላይ በነበሩበት ወቅት፤ የፖለቲካ አመራር የሚሰጥ አካል ባለመኖሩ፤ በናንተ በኩል በፍጹም ታማኝነትና ቀራጥነት ያደረጋችሁት ተግባር ከልብ እናደንቃለን።

ላለፉት 15 ወራት ከሰሜን አሜሪካ እስከ አውሮፓና አውስትራሊያ፤ ከካናዳ እስከኤሽያና ደቡብ አፍሪካ የድጋፍ ሰጪ ምክር ቤቶች እንዲቋቋሙ አድርጋችኋል። እነዚህ ምክር ቤቶችም በአህጉር ደረጃ የሚመሯቸውን ግለሰቦች ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ እንዲመርጡ፤ በእነሱም አማካኝነት የዲፕሎማሲያዊ ትግሉ እንዲጠናከር በማድረግ አደራችሁን ተወጥታችኋል። በተለያዩ ጊዜያት ባደረግናቸው ህዝባዊ ስብሰባዎችና የሻማ ማብራት ዝግጅቶች ላይ፤ ቅንጅትን በመወከል ተገኝታችሁ ህዝቡን ከዳር እስከዳር ቀስቅሳችኋል።

ምንም እንኳን የቅንጅት ድረ-ገጽ በጥቂት ግለሰቦች እጅ ወድቆ አፍራሽ የሆኑ ተግባራት ሲፈጸሙበት የቆየ ቢሆንም፤ የቅንጅትን አርማ በግል ስማቸው ቢያስመዘግቡም፤ ከህዝብ የተሰበሰበውን ገንዘብ ደብዛውን ቢያጠፉትም፤ አያንዳንዳችሁን በተናጠል፤ ሁላችሁንንም በቡድን ቢያጠቋችሁም፤ የስም ማጥፋት ዘመቻ ቢያካሂዱባችሁም፤ ይህንን ሁሉ ተቋቁማችሁ ለመሪዎቻችን መፈታት የምስራች አብቅታችሁናል... ከናንተም ፅናትን ተምረናልና፤ ከልብ እናመሰግናለን።

የኢትዮጵያ ህዝብ ድምፁን እንዳያሰማ በተነፈገበት ወቅት እናንተ ልሳን ሆናችሁ፤ ፍቅርና አንድነትን ሰብካችኋልና ስላደረጋችሁልን መልካም ነገር ሁሉ ምስጋናችን ይድረሳችሁ። የቅንጅትን ዲሞክራሲያዊ አሰራር መርህ በማድረግ፤ የድጋፍ ድርጅቶች ወደፊት እንድራመድ አድርጋችሁናልና እናመሰግናለን። ከምንም ነገር በላይ ደግሞ በቅንጅት ደጋፊዎች መካከል ቅንነትና መቻቻል እንዲጎለብት፤ ላመኑት ነገር በጽናት መቆምን አስተምራችሁናል። የሰላማዊ ትግልን ጠመዝማዛ መንገዶች ስትጓዙ፤ በመንገዳችሁ ላይ ሁሉ እንቅፋትና ሴራ ሲሰራባችሁ ሁሉንም በትእግስት በመቻል፤ ትኩረታችሁን መሪዎቻችን በሰጧችሁ ሃላፊነት ላይ በማድረግ ለዛሬው፤ ወርቃማ ቀን አድርሳችሁናልና እናመሰግናለን።

ይህንን ሁሉ ሃላፊነት ተወጥታችሁ፤ ለኛና ለታሰሩት መሪዎቻችን ቤዛ ሆናችሁ፤ አሁን ደግሞ መሪዎቻችን የሰጧችሁን አደራ በክብር ለማስረከብ በመብቃታችሁ፤ ለድርጅቱና ለመሪዎቻችን ያላችሁን ፍጹም ታማኝነት ያመለክታል። በአጠቃላይ አደራችሁን በሚገባ ለመወጣታችሁ፤ ላለፉት አስራ አምስት ወራት ስንከተላችሁ የነበርን ኢትዮጵያዊያን ህያው ምስክሮች ነን። ጊዜያዊ ስልጣንና የግል ዝና ሳያታልላችሁ፤ አደራችሁን በክብር በማስረከባችሁ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አዲስ ምዕራፍ በመክፈታችሁ፤ ኮርተንባችኋል። እናንተ መልካም ነገርን ስትፈጽሙ፤ እኛም ከማመስገን ባሻገር እውነተኛ ምስክርነታችንን ለታሪክ እንሰጣለን፤ ይህንን ምስክርነት በኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማና በአምላካችን ስም በሃቅ ሰጥተናል።

ስላደረጋችሁት ሁሉ እናመሰግናለን።

ኢትዮጵያን አምላክ ይባርክ!

የአትላንታ የቅንጅት ቻፕተር